# የመደመር የወደፊት ጉዞና ተግዳራቶቹ

ሩፋኤል ሰለሞን

2010 ዓ.ም. ባገራችን ትልቅ ትአምር የታየበት ዓመት ነው። ይህ የሚያስብለውም

1. የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ ይደርስበት የነበረውን ግፍና ስቅያት በወኔ የተቋቋመበት ዓመት በመሆኑ
2. ሰቆቃውና ስቃዩን ከንግዲህ በቃኝ በማለት ፍርሃቱን አሽቀንጥሮ በመጣል ወያኔን ያለፋታ የተፋለመበት ወቅት ስለሆነ
3. የወያኔ ስርዓት የፈጠረውን እርስ በርስን የመጠራጠርና ያገሪቱን ጉዳይ በማጥበብ ያካሂድ የነበረውን የዘውገኛና የተናጠል ትግል እርግፍ አድርጎ በመተው "ያማራ ደም ደሜ ነው"፣ "የኦሮሞ ደም ደሜ ነው" በማለት በኅብረት የተቀናጀ ትግል ያካሄደበት ዓመት ስለሆነ ነው።

በመሆኑም የፋኖና የቄሮ መደራጀትን ፈጥሮ በውስጡ የቲም ለማና የቲም ገዱ በውስጥ በማብቀል ፈጽሞ ነቅ ሊል የማይችል ይመስል የነበረውን የወያኔ ኢህአዴግን አሽቀንጥሮ በመጣል በዶክተር ዓቢይ አህመድ የሚመራውን መንግሥት ለማቋቋም ችሏል። ጠቅላይ ሚኒስቴር ዓቢይ አህመድ ለኢህአዴግ ሊ/መንበርነትና ለኤፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስተሪነት ስልጣን ሲመረጡ በፓርላማ ለመጀመሪያ ጊዜ ካደረጉት ንግግር ጀምሮ አሁን ድረስ በሚሉት አባባልና በሚወስዱት እርምጃዎች ያለማጋነን ያገሪቱ ሕዝብ በሙሉ በደስታ ተቀብሏቸዋል። አድናቆቱ ካገሪቱ ድንበር ዘሎ በመላው ዓለም እየተንጸባረቀ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ማድነቅ ብቻ ሳይሆን ከዚህ በፊት ገጥሞት የማያውቅ ተስፋ እንዲሰንቅ ሆኗል። እስካሁን እንደታየው ይህ ተስፋ እየጎመራ እንደሚሄድ ምንም ጥርጥር የለም። ህዝቡም እስካሁን የተካሄደውን ለውጥና ወደፊት የሚቀጥለውን ተስፋ ሰጪ ጉዞ በሕብረት፣ እንደ አንድ ሰው ሆነው እንደሚጠብቀው በግልጽ እያሳየ ነው።

ይህ የመደመር አመርቂ ለውጥ ከፊቱ የሚጠብቁት ተግዳራቶች አሉ። ይህ አመርቂ ለውጥ ገና በሁለት እግሩ አልቆመም። ከፊቱ ከተደቀኑት ተግዳራቶች ዋነኛውና አደገኛው ለውጡን እንደ ቅስፈት የሚያዩት ሃይሎች ናቸው። ይኸው የጥንቱ የወያኔ ኢህአዴግ አመራሮችና የጭቆና መሳሪያቸው ጠ/ ሚኒስቴር ዓቢይ ሃላፊነቱን ከተረከቡበት ቀን ጀምረው ፊት ለስልጣናቸውና ለቅጥ የለሹ ሙስናቸው ማእከል ከነበረው አዲስ አበባ ወጥተው መቐለ ውስጥ መሽገዋል። በዚህ ወቅት ሁሉ መቋጫ የሌለው ስብሰባና ሴሚናሮች እያደረጉ ይገኛሉ። ይህ ሁሉ ስብስብና ጉባኤ ይህን ለውጥ ወደፊት ለማራመድ

እንዳልሆነ ከአሁኑ መገንዘብ አስፈላጊ ነው። ይህን ቀልባሽ ሃይል በመቋቋም ለውጡን ወደፊት ለማስቀጠል መልሱ በተጠንቀቅ መቆም፣ በመደመር ኀብረቱን ማጠናከርና ስርአቱን ከወያኒያዊ አመለካከት ማጽዳት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የለውጡን ኃይል በመደመር ማጠናከር ነው። መደመር ግን እንዲሁ በምኞት የሚመጣ አይደለም። በለውጥ ኃይሉ ውስጥ ያሉ ልዩነቶችን እየቀረፉ አንድነትን ማጎልበት ነው። የለወጡ ኃይሎች ላለፉት ከ 66 ዓብዮት ጀምሮ በትግል ውስጥ የነበሩና ከነበሩት የተለያዩ የትግል ስልቶች ሳቢያ በመሃላቸው መቃቃር የነበራቸው፣ ገሚሶቹም ደም የተቃቡ ናቸው። እኒህ የለውጥ ኃይሎች በእውነትም እንዲደማምሩ የግድ ይቅር ይቅር መባባል አለባቸው። በዚህ ጉዳይ ላይ ፍቱን የሆነው መንገድ በመሃላቸው የእርቅና የሰላም ጉባኤ ማካሄድ ነው። ይህ ነው የተፈተነ አካሄድ። እርቅና ሰላም እስካልተፈጠረ ድረስ ግን ሙሉ መተባበር አይኖርም። ፍላጎቱ ቢኖርም ገላህን ሰደህ አብረህ አንድ ኃይል መሆኑ ይቀርና በጥርጣሬ የታጀበ የይሉኝታ ጓድኝነት ተፈጥሮ ሁሌ እንቅፋት እየሆነ ይቀጥላል።

ይ 44 ዓመት ታሪካችን ያሳየንና ለጸረ ለወጥ ኃይሎች መጫወቻ እንድንሆን ያደረገን ይኸው ነው። የእርቅና ሰላም ጉባኤ አምራጭ የሌለው መፍትሄ ነው። ለዚህም የጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር ዓቢይን አመራር ይጠይቃል።

በመደማመር፣ በአንድነት ለውጡን ወደፊት እናራምድ!

ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን በአንድነት እንመስርት!